# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ፪ሺ፪ ዓ.ም.

16th Year No.14
ADDIS ABABA 5th March 2010



ደንብ ቁጥር ፻፸፫/፪ሺ፪
የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......ገጽ ፭ሺ፪፻
የአገልግሎት ክፍያዎች ሠንጠረዥ........ገጽ ፭ሺ፪፻፮

Regulation No.173/2009
Classification of Tourist Facilities Council of Ministers Regulation...........Page 5200
Schedule of Fees..................Page 5206


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፸፫/፪ሺ፪ ስለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፸፫/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት ሆቴል፣ ሞቴል፣ ሎጅ፣ ፔንሲዮን ወይም ሬስቶራንት ነው፤

፪/ "ቱሪስት" ማለት በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሌላ አካባቢ በመጓዝ በደረሰበት አካባቢ በማንኛውም ዓይነት ክፍያ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ሳይሰማራ ከ፳፬ ሰዓት ላላነሰና ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው፤

፫/ "የደረጃ ምደባ" ማለት ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ፔንሲዮኖችና ሬስቶራንቶች የአገልግሎት ጥራት ደረጃቸውን ለመጠበቅ ይዞታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ የሚመዘኑበት ሥርዓት ነው፤

፬/ ‹‹ሆቴል›› ማለት የመኝታ፣ የምግብ፣ የመጠጥና እንደ አስፈላጊነቱም የመዝናኛ፣ የስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

*Council of Ministers RegulationNo. 173/2009*

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON CLASSIFICATION OF TOURIST FACILITIES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Classification of Tourist Facilities Council of Ministers Regulation No. 173/2009".

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ "tourist facility" means a hotel, motel, lodge, pension or restaurant;

2/ "tourist" means any person visiting a place other than that in which he has his usual place of residence, for at least 24 hours, but not more than one year, and whose main purpose of visit is other than following a remunerated occupation;

3/ "classification" means the system of rating to assure quality standards of the services of hotels, motels, lodges, pensions and restaurants;

4/ "hotel" means an establishment offering lodging, food, and beverage and, as may be needed, recreational, conference and similar facilities to tourists and other clients;


ያንዱ ዋጋ Unit price 3.60

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፭/ "ሞቴል" ማለት የመኝታ፣ የመኪና ማቆሚያና እንደ አስፈላጊነቱ የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን በከተማ፣ ከከተማ ውጭና በአውራ ጎዳና ዳር ላይ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፮/ "ሎጅ" ማለት የመኝታ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን፣ እንደአስፈላጊነቱም የመዝናኛ፣ የስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን በተፈጥሮ አካባቢ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፯/ "ፔንሲዮን" ማለት የመኝታና የቁርስ አገልግሎት ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፰/ "ሬስቶራንት" ማለት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፱/ "የምስክር ወረቀት" ማለት በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሥራ ላይ ለተሠማራ ድርጅት የሚሰጥ የደረጃ መለያ ማስረጃ ነው፤

፲/ "ዓርማ" ማለት ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሚደረግ የደረጃ ምደባ መሠረት የሚሰጥ መለያ ነው፤

፲፩/ "አገልግሎት" ማለት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለተጠቃሚዎች በክፍያ የሚሰጠው መስተንግዶ ነው፤

፲፪/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፲፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ፫. ዓላማ

የዚህ ደንብ ዓላማ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የአገልግሎት ጥራት እንዲያሻሽሉና ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲኖራቸው ለማስቻል ማገዝና መቆጣጠር ይሆናል።

## ፬. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙና ደረጃ ሊመደብላቸው በሚገባ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፭. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃዎች

፩/ የተወሰነውን መሥፈርት የሚያሟሉ ሆቴሎች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፦

ሀ) ባለ አምስት ኮከብ + ዴሉክስ ሆቴል፤

ለ) ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል፤

ሐ) ባለ አራት ኮከብ ሆቴል፤

መ) ባለ ሦስት ኮከብ ሆቴል፤

ሠ) ባለ ሁለት ኮከብ ሆቴል፤

ረ) ባለ አንድ ኮከብ ሆቴል፤

ሰ) ተመራጭ ሆቴል።

5/ "motel" means an establishment which is located in a town, a suburb or alongside a highway and offering lodging, vehicle parking and, as may be needed, food and beverage to tourists and other clients;

6/ "lodge" means an establishment located in a natural surrounding and offering lodging, food and beverage, and as may be needed, recreational, conference and similar services to tourists and other clients;

7/ "pension" means an establishment offering lodging and breakfast services to tourists and other clients;

8/ "restaurant" means an establishment offering food and beverage services to tourists and other clients;

9/ "certificate" means a certificate given to a tourist facility to certify its classification;

10/ "emblem of standard" means an insignia given to a tourist facility to show its classification;

11/ "service" means service provided by a tourist facility to customers in considerations of payment;

12/ "Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minister of Culture and Tourism, respectively;

13/ "person" means any natural or juridical person;

14/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Objective

The objective of this Regulation shall be to support and regulate tourist facilities so that they can improve quality of service and maintain internationally acceptable standards.

## 4. Scope of Application

This Regulation shall be applicable to all tourist facilities in Ethiopia that have to be classified.

## 5. Classification of Tourist Facilities

1/ Hotels that meet the prescribed criteria shall be classified as follows:

a) five star + deluxe hotel;

b) five star hotel;

c) four star hotel;

d) three star hotel;

e) two star hotel;

f) one star hotel;

g) recommended hotel.

፪/ የተወሰነውን መሥፈርት የሚያ ሟሉ ሎጆች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-
ሀ) ባለ አምስት ኮከብ ሎጅ፤
ለ) ባለ አራት ኮከብ ሎጅ፤
ሐ) ባለ ሦስት ኮከብ ሎጅ፤
መ) ባለ ሁለት ኮከብ ሎጅ፤
ሠ) ባለ አንድ ኮከብ ሎጅ፤
ረ) ተመራጭ ሎጅ፡፡

፫/ የተወሰነውን መሥፈርት የሚያ ሟሉ ሞቴሎች በሚከተሉት ደረጃ ዎች ይመደባሉ፡-
ሀ) ባለ አምስት ኮከብ ሞቴል፤
ለ) ባለ አራት ኮከብ ሞቴል፤
ሐ) ባለ ሦስት ኮከብ ሞቴል፤
መ) ባለ ሁለት ኮከብ ሞቴል፤
ሠ) ባለ አንድ ኮከብ ሞቴል፤
ረ) ተመራጭ ሞቴል፡፡

፬/ የተወሰነውን መሥፈርት የሚያሟላ ፔንሲዮን "ሪኮሜንድድ ፔንሲዮን" ተብሎ ይመደባል፡፡

፭/ የተወሰነውን መሥፈርት የሚያሟሉ ሬስቶራንቶች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-
ሀ) ባለ አምስት ኮከብ ሬስቶራንት፤
ለ) ባለ አራት ኮከብ ሬስቶራንት፤
ሐ) ባለ ሦስት ኮከብ ሬስቶራንት፤
መ) ባለ ሁለት ኮከብ ሬስቶራንት፤
ሠ) ባለ አንድ ኮከብ ሬስቶራንት፤
ረ) ተመራጭ ሬስቶራንት፡፡

፮/ ሚኒስቴሩ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በመውሰድ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለመመደብ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

፯/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ያወጣው መመሪያ በተጠቃሚዎችና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ በሰፊው እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

**፮. ደረጃን የማስመደብ ግዴታ**

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፭ ከተዘረዘሩት ደረጃዎች በአንዱ ሊመደብ የሚችል የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው የድርጅቱን ደረጃ የማስመደብ ግዴታ አለበት፡፡

**፯. ማመልከቻ ስለማቅረብ**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተደነገገው ግዴታ የሚመለከተው ሰው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ሥራ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የደረጃ ምደባ እንዲደረግለት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ የምስክር ወረቀትና ዓርማ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የደረጃ ለውጥ ወይም የንግድ ድርጅት ስያሜ ለውጥ ሲያደርግ የእንደገና ምደባ እንዲደረግለትና የምስክር ወረቀትና ዓርማ በምትክነት እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ጥያቄ ሲቀርብለት በ፴ ቀናት ውስጥ ምላሹን ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

2. Lodges that meet the prescribed criteria shall be classified as follows:
a) five star lodge;
b) four star lodge;
c) three star lodge;
d) two star lodge;
e) one star lodge;
f) recommended lodge.

3/ Motels that meet the prescribed criteria shall be classified as follows:
a) five star motel;
b) four star motel;
c) three star motel;
d) two star motel;
e) one star motel;
f) recommended motel.

4/ A pension that meets the prescribed criteria shall be classified as "recommended pension".

5/ Restaurants that meet the prescribed criteria shall be classified as follows:
a) five star restaurant;
b) four star restaurant;
c) three star restaurant;
d) two star restaurant;
e) one star restaurant;
f) recommended restaurant.

6/ The Ministry shall adopt international standards and issue directives providing for the classification of tourist facilities pursuant to this Article.

7/ The Ministry shall take necessary measures to disseminate, to users and the public in general, directives issued under sub-article (6) of this Article.

**6. Requirement of Classification**

Any person that operates a tourist facility which may fall under any of the classifications listed in Article 5 of this Regulation, shall have the obligation to have the facility classified.

**7. Submission of Application for Classification**

1/ Any person to whom the provisions of Article 6 of this Regulation is applicable shall submit an application for classification of the tourist facility within one year from commencement of operation.

2/ A tourist facility that has been issued with a certificate and emblem pursuant to this Regulations shall, in the event of change in its standard or trade name, submit an application to the Ministry for reclassification and issuance of substitute certificate and emblem.

3/ The Ministry shall notify its decision to the applicant within 30 days of receipt of an application pursuant to sub-article (1) or (2) of this Article.

**፰. <u>የምስክር ወረቀትና ዓርማ እንዲታይ ስለማድረግ</u>**

ማንኛውም በደረጃ የተመደበ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሚኒስቴሩ የተሰጠውን የምስክር ወረቀትና ዓርማ በድርጅቱ ዋና መግቢያ ጎልቶ ሊታይ በሚችልበት ሥፍራ ማስቀመጥ አለበት::

**፱. <u>የደረጃ ምደባ እንደገና ስለማከናወን</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ ደረጃ ለተመደበላቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በየሦስት ዓመቱ በአዲስ መልክ የደረጃ ምደባ ያከናውናል::

፪/ የእንደገና ምደባው ተግባር ለድርጅቱ ሥራና ለተጠቃሚው አመቺ በሆነ ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ወኪሉ ለሚቀርብለት ጥያቄ ተገቢውን መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት::

**፲. <u>የደረጃ ምደባ መዝገብ</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን የደረጃ ምደባ መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል::

፪/ ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የንግድ ስሙ ወይም የደረጃ ምደባው ሲለወጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተደረገው ምዝገባ መስተካከል አለበት::

፫/ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የደረጃ ምደባ መዝገብ ለሕዝብ ተደራሽ ይደረጋል::

**፲፩. <u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>**

፩/ ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተመደበለትን ደረጃ ጠብቆ የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ሚኒስቴሩ ቁጥጥር ያካሂዳል::

፪/ የቁጥጥሩ ተግባር ለድርጅቱ ሥራና ለተጠቃሚው አመቺ በሆነ ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ወኪሉ ለሚቀርብለት ጥያቄ ተገቢውን መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት::

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቁጥጥር የሚያደርገው በራሱ አነሳሽነት ወይም የተገልጋዮችን ቅሬታ ወይም አስተያየት መነሻ በማድረግ ይሆናል::

፬/ ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተገልጋዮችን ቅሬታና አስተያየት ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል::

**፲፪. <u>የምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ</u>**

፩/ ምደባ የተደረገለት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በምስክር ወረቀቱ ላይ ለተመለከተው ምደባ የተቀመጠውን የደረጃ መስፈርት ያልጠበቀ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ በሚወስነው ተገቢ የሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን እንዲያስተካክል በጽሑፍ ትዕዛዝ ይሰጠዋል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ አክብሮ ያልፈጸመ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተሰጠው የምስክር ወረቀት ይሰረዛል:: የስረዛው ውሳኔም ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ በጽሑፍ እንዲደርሰው ይደረጋል::

፫/ የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ውሳኔ የተሰጠበት ድርጅት ባለቤት ወይም ወኪሉ የምስክር ወረቀቱ ሊሰረዝ አይገባም የሚል ከሆነ ቅሬታውን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ማቅረብ ይችላል::

፬/ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ወኪሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ቅሬታውን ካላቀረበ ወይም ያቀረበው ቅሬታ ተመርምሮ ውድቅ ከተደረገ የምስክር ወረቀቱ መሠረዝ ይጸናል::

፭/ ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የምስክር ወረቀት መሰረዙን አመቺ በሆነ የመገናኛ ዘዴ ለሕዝብ ያሳውቃል::

**8. <u>Display of Certificate and Emblem</u>**

Any classified tourist facility shall display, at a prominent spot of its main entrance, the certificate and emblem issued to it by the Ministry.

**9. <u>Reclassification</u>**

1/ The Ministry shall carry out a reclassification of all classified tourist facilities every three years.

2/ The reclassification process shall be carried out at a time convenient to the facility and its clients, and the owner of the facility or his agent shall answer all queries presented to him.

**10. <u>Register of Classification</u>**

1/ The Ministry shall organize and maintain a register of classification of tourist facilities.

2/ When an alteration is made to the trade name of a tourist facility, or when its classification is changed, entries in the register referred to in sub-article (1) of this Article shall be adjusted accordingly.

3/ The register of classification of tourist facilities shall be made accessible to the public.

**11. <u>Inspection</u>**

1/ The Ministry shall inspect any classified tourist facility in order to ensure that its standard is maintained.

2/ The inspection shall be conducted at a time convenient to the tourist facility and its clients, and the owner or his agent shall be obliged to answer enquires in relation to the inspection.

3/ The Ministry shall undertake inspection under this Article on its own initiatives or on the basis of customers' complaints or comments.

4/ The Ministry shall design a system for handling complaints and comments of customers of tourist facilities.

**12. <u>Cancellation of Certificate</u>**

1/ Where a tourist facility fails to maintain the standard required for the classification indicated on its certificate of classification, a written order shall be issued to it to rectify the irregularities within a reasonable period of time to be specified by the Ministry.

2/ The certificate of classification of a tourist facility that has failed to comply with an order issued under sub-article (1) of this Article shall be cancelled. Such decision shall be communicated, in writing, to the tourist facility.

3/ If the owner of a tourist facility, the certificate of which has been cancelled, or his agent believes the cancellation to be unjustified, he may submit his complaint in accordance with Article 17 of this Regulation.

4/ If the owner of a tourist facility or his agent fails to submit his complaint in accordance with sub-article (3) of this Article or the complaint is rejected after its examination, the cancellation of the certificate shall become effective.

5/ The Ministry shall publicize the cancellation of the certificate of a tourist facility through appropriate media.

## ፲፫. የምስክር ወረቀትንና ዓርማን ስለመመለስ

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ወይም ሥራውን ያቆመ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የምስክር ወረቀቱንና ዓርማውን ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት::

## ፲፬. ምትክ የምስክር ወረቀትና ዓርማ ስለመስጠት

ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም ዓርማ ከተበላሸ ወይም ከጠፋና ስለመጥፋቱ ድርጅቱ ማረጋገጫ ለሚኒስቴሩ ካቀረበ ምትክ ይሰጠዋል::

## ፲፭. የአገልግሎት ክፍያዎች

ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የደረጃ ምደባና እንደገና ምደባ እና የምስክር ወረቀትና ዓርማ ለመስጠትና ለመተካት ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይፈፀማል::

## ፲፮. ግዴታዎችን ስለመፈፀም

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ከተዘረዘሩት ደረጃዎች በአንዱ ሊመደብ የሚችል ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮፣ ፰፣ ፱(፪)፣ ፲፩(፪) እና ፲፭ የተጠቀሱትን ግዴታዎች መፈፀም አለበት::

፪/ ሚኒስቴሩ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት ግዴታዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል::

## ፲፯. ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ

፩/ ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የደረጃ ምደባንና የእንደገና ምደባን እና የምስክር ወረቀት ስረዛን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምር ኮሚቴ ያቋቁማል::

፪/ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በተሰጠ የደረጃ ምደባ ወይም የእንደገና ምድባ ውሳኔ ወይም በምስክር ወረቀት መሰረዝ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ፴ ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተቋቋመው ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል::

፫/ ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ በ፵፭ ቀናት ውስጥ መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለሚኒስትሩ ያቀርባል::

## ፲፰. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፱. የተሻረ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፹፯ በዚህ ደንብ ተሽሯል::

## ፳. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዘህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ በተሻረው ደንብ መሠረት ተመድበው የነበሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ይህ ደንብ እንደጸና እንደገና ይመደባሉ::

## 13. Returning of Certificate and Emblem

A tourist facility, the certificate of which has been cancelled in accordance with Article 12 of this Regulation or which has ceased its operation, shall return its certificate and emblem to the Ministry.

## 14. Replacement of Certificate and Emblem

Where a certificate or an emblem issued to a tourist facility has been damaged or lost, a replacement shall be given to the tourist facility, provided that evidence is presented to the Ministry in the case of a loss.

## 15. Fees

Fees to be paid for classification and reclassification of tourist facilities and for the issuance and replacement of certificates and emblems shall be as prescribed in the Schedule attached to this Regulation.

## 16. Compliance

1/ Any tourist facility that may fall under any of the classifications listed in Article 5 of this Regulation shall comply with the requirements prescribed in Articles 6, 8, 9(2), 11(2) and 15 of this Regulation.

2/ The Ministry shall, in collaboration with other relevant executive organs, ensure compliance of the requirements referred to in sub-article (1) of this Article.

## 17. Handling of Grievances

1/ The Ministry shall establish a committee to investigate grievances relating to the classification and reclassification of tourist facilities and the cancellation of certificates.

2/ Any person aggrieved by the classification or reclassification of a tourist facility or the cancellation of a certificate may, within 30 days, lodge his complaints with the committee established in accordance with sub-article (1) of this Article.

3/ The Committee shall investigate the complaint and submit its recommendation to the Minister within 45 days.

## 18. Power to Issue Directives

The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

## 19. Repeal

The Council of Ministers Regulation No.209/1995 is hereby repealed.

## 20. Transitory Provisions

Tourist facilities classified pursuant to the Regulation repealed under Article 19 of this Regulation shall be re-classified following the effective date of this Regulation.

፳፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

21. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 5th day of March, 2010.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## የአገልግሎት ክፍያዎች ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ዓይነት | ምደባ ወይም እንደገና ምደባ | ዓርማ (ሲሰጥ/ሲተካ) | የምስክር ወረቀት (ሲሰጥ/ሲተካ) |
|---|---|---|---|---|
| | | (ብር) | (ብር) | (ብር) |
| ፩ | ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆችና ፔንሲዮኖች | | | |
| ፩.፩ | እስከ ፳፭ ክፍሎች | ፩ሺ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |
| ፩.፪ | ከ፳፮ እስከ ፶ ክፍሎች | ፩ሺ፭፻ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |
| ፩.፫ | ከ፶፩ እስከ ፩፻ ክፍሎች | ፩ሺ፯፻፶ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |
| ፩.፬ | ከ፩፻፩ እስከ ፪፻ ክፍሎች | ፪ሺ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |
| ፩.፭ | ከ፪፻፩ እስከ ፬፻ ክፍሎች | ፪ሺ፭፻ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |
| ፩.፮ | ከ፬፻ በላይ ክፍሎች | ፪ሺ፯፻፶ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |
| ፪ | ሬስቶራንት | ፭፻ | ፩ሺ፪፻ | ፶ |

## SCHEDULE OF FEES

| No. | Types of Tourist Facility | Classification or Reclassification | Emblem (Issuance or Replacement) | Certificate (Issuance or Replacement) |
|---|---|---|---|---|
| | | (Birr) | (Birr) | (Birr) |
| 1 | Hotels, Motels and Lodges | | | |
| 1.1 | up to 25 rooms | 1000 | 1200 | 50 |
| 1.2 | from 26 to 50 rooms | 1500 | 1200 | 50 |
| 1.3 | from 51 to 100 rooms | 1750 | 1200 | 50 |
| 1.4 | from 101 to 200 rooms | 2000 | 1200 | 50 |
| 1.5 | from 201 to 400 rooms | 2500 | 1200 | 50 |
| 1.6 | above 400 rooms | 2750 | 1200 | 50 |
| 2 | Restaurant | 500 | 1200 | 50 |